

# የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሺነሪ ጉዞ

- ጳውሎስና በርናባስ በዮሐንስ ማርቆስ ምክንያት በመካከላቸው አለመግባባት ስለተፈጠረ ተለያዩ። ይህ ወጣት ቀደም ብሎ ከእነርሱ ጋር ያገለግል ነበር። ሆኖም ትቷቸው ወደኢየሩሳሌም ተመለሰ። በርናባስ የወንድሙ ልጅ ለሆነው ለዮሐንስ ማርቆስ ሁለተኛ እድል እንዲሰጠው ይፈልጋል። ጳውሎስ ደግሞ በሚቀጥለው የወንጌል ጉዟቸው አብሯቸው እንዲሆን አይፈልግም። በዚህ ምክንያት በርናባስና ዮሐንስ ማርቆስ በአንድ አቅጣጫ ሲጓዙ ጳውሎስና ሲላስ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ መጓዝ ጀመሩ።
  ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ሌሎች ሁለት ሰባኪዎችም አብረዋቸው ነበሩ። እነርሱም ጢሞቴዎስ የሚባለው ወጣት ክርስቲያንና ሐኪሙ ሉቃስ ናቸው።

- የነጳውሎስ ቡድን ተሰሎንቄ ወደምትባል የወደብ ከተማ ደረሰ። በዚያም ጳውሎስ ለሶስት ሰንበቶች በአይሁድ ምኩራብ ሰበከ። ብዙ አይሁዳውያንና ግሪኮች በጳውሎስ ስብከት አመኑ። ሆኖም ያላመኑ አይሁዳውያን ጠላቶቹ ሆነው በእርሱ ላይ አመፅን ያነሳሱ ነበር። ከዚህ የተነሳም ጳውሎስና ሲላስ በጨለማ ከከተማይቱ ለመውጣት ተገደዱ።

- ቤርያ ተብሎ ወደሚጠራ አካባቢም ሄዱ። በዚያም ስብከቱን የሰሙ የቤርያ ሰዎች አመኑ። ሆኖም ጳውሎስ የሚናገረው ነገር ከቅዱሳት መፃሕፍት ጋር እንደሚስማማ እለት እለት ይመረምሩ ነበር።
  በእርግጥም የነጳውሎስ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ ነበር። ምክንያቱም በነጳውሎስ እየተጠቀመ ያለው እግዚአብሔር ነበር መፅሐፍ ቅዱስን በሰዎች እንዲፃፍ ያደረገው። መፅሐፍ ቅዱስ ስለቤርያ ሰዎች ሲናገር በተሰሎንቄ ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ እነርሱ እንደሚሻሉ ይናገራል። ምክንያቱም የጳውሎስ ስብከት ትክክለኛ እንደሆነ ወይንም እንዳልሆነ ይመረምሩ ነበርና።
  በተሰሎንቄ የነበሩ አይሁድ ወደቤርያ መጥተው በጳውሎስና በሲላስ ላይ ሰዎችን በክፉት ማነሳሳት ያዙ። በዚህ ምክንያት በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ጳውሎስን ወደ አቴንስ ላኩት። ሆኖም ሲላስና ጢሞቴዎስ በቤርያ ቀርተው ጳውሎስን መጠባበቅ ጀመሩ።

*የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሺነሪ ጉዞ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17፡ 1 – 15 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com